# ኢትዮጵያችን

*አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

*ኢትዮጵያችን ቅጽ 2 ቁጥር 2* *ጥቅምት ፲፮ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ.ም.*


## ቀጣዩ መንግሥት

(*የድምጽ ቅጅውን ለማድመት እዚህ ይጫኑ።* https://www.youtube.com/watch?v=pTyIVecmdJE)

*በሀገራችን ኢትዮጵያ ለዴሞክራሲ መብትና ለሕግ የበላይነት ብሎም ለጥሩ መንግስታዊ አስተዳደር በተደረጉ ትግሎች አታጋይ ድርጅቶች ብቅ ማለት ከጀመሩ በትንሹ ወደ*40 *ዓመት ይወስደናል። ብሔራዊ አጀንዳ ይዘው ሕዝብን ያታገሉ እንዳሉ ሁሉ በዘር የተደራጁም ብቅ ማለታቸው ይታወቃል። በወያኔ/ህወሀት አገዛዝ ዘመን እጅግ በርካታ ህብረ ብሔርና የጎሳ ድርጅቶች የወያኔን አገዛዝ በመቃወም የተቻላቸውን አስተዋጽዎ አበርክተዋል እያበረከቱም ይገኛሉ። ለሀገራችን ኢትዮጵያ ድምጻቸውን የሚያሰሙ የፖለቲካ ድርጅቶች በጋራ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ በመምከር ሁሉንም ታጋይ ኃይሎች የሚያቅፍ ትብብር አለመፍጠራቸው ትግሉን እጅጉን እንደጎዳው ይታያል።*

*የመጨረሻው ሰዓት ደርሷል እንላለን። ይህ የመጨረሻ ሰዓት ግን ምን ይዞ እንደሚመጣ የተዘጋጀን አይደለንምና ግራ ገብቶናል። ለሀገራችን ስንል በጋራ መሰለፍን በተግባር አላሳየነውም። ጊዜ እየቀደመን ሳይሆን በእርግጥ ቀድሞናል። ሀገራችን ኢትዮጵያ ያጋጠሚትን ወርቃማ ጊዜዎች ባህሪያችን እንደ መዳብ ቀጥሮ ዛሬም መልህቋ እንደተበጠሰ መርከብ ወዴት እንደሚኬድ በተስፋ ከመንዝ በቀር ሌላ አይታይም። የተሰጠንን* 26 *የመከራ ዘመን ተጠቅመን መጠናከርና መሪ ኮከብ መፍጠር አልቻልንም።*

*በ*1997 *ዓ.ም. ያበቃለትን ወያኔ፣ የተገኘውን "የምርጫ ድል"፣ ለግብ ለማብቃት ከመዋደቅ ይልቅ ሕዝብን በመክዳት፣ ለሙት ቀን አድማ ነፍስ በመዝራት* 13 *ዓመት ዕድሜ ተሰጠው። መስዋዕትነት ተፈርቶ ትግል ባዶ መሆኑን አልተገነዘብንምና። መስዋዕትነት ተከፍሎም ትግል ሊኮላሽ እንደሚችል ከራሳችን ታሪክ አልተማርንምና። ሕዝብ ይታገላል፣ ተማሪዎች ቀዳሚ በመሆን ሰልፍ ይወጣሉ፣ ወጣቶችና ሴቶች እህቶቻችን ማንንም ሳይፈሩ ለሀገርና ለሕዝብ ድምጻቸውን ያሰማሉ። ግን እንዲህ ብቅ የሚሉ ተቃውሞዎችን አሰባስቦ ሊመራና ትግሉን ሊያቀናጅ የሚችል ኃይል "ዳግም አይፈጠርብሽ" የሚል እርግማን ያለባት ይመስል ሀገራችን ልትወልድ አልቻለችም።*

*በዘመነ ቅኝ ግዛት የነበሩ የአያት፤ የአባቶች የጀግንነት ታሪክ ለሀገሩ፣ ለሰንደቅ ዓላማውና ለሕዝቡ ጽኑ ተሟጋች ኃይል ሊፈጥር ቢችልም ቀጣይነት ሳይኖረው ተሽመድምዷል። የደርግ የጅምላ ጭፍጨፋና የአንድ ትውልድ ግድያ የታሪክ ቅብብሎሽን ገመድ የበጠሰው ይመስል ትውልድ ቢተካም የሀገርና የሕዝብ መሪ አልበቀለም። ድፍረት አይሁንብንና ጀግንነት በፍርሃት፣ እኛነት በእኔነት፣ ሀገር በባዕድ ተተኩ ብንል ስህተት አይመስለንም።*

*ኢትዮጵያን በአንድነት ይዞ ሊጓዝ ዘር፣ ጎሳ፣ ቋንቋ፣ ክልል፣ ሃይማኖት ሳይከፋፍለው የተነሳው የያ ትውልድ ኃይል የራሱ አመራር ብቃት ታክሎበት ሀገራችን የገጠማት የፋሽስታዊ አገዛዝ በትር ዛሬ*

ለደረስንበት ሀገርና ትውልድ መሽመድመድ የራሱ አስተዋጽዖ እንዳለው አይካድም። አሁንም ሀገር በአጥፊዎቿ እየታመሰች ማየት ብቻ ሳይሆን ቀጣይ መንግሥት ለመሆን ጎልተው የታዩት መበታተኗን የሚወዱ መሆናቸውን ስናይ ችግሩ ያለው ከአንድነት ኃይሉ ወይስ ሌላ? ያሰኛል።

ለማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ግልጽ ሊሆን የሚገባው ወያኔ ከራሱ ውስጣዊ ችግር ባሻገር ሊነቀንቀው የተዘጋጀ የፖለቲካ ድርጅት ዛሬም በጥያቄ ነው። ሆኖም ግን የሀገራችንን ሰንደቅ ዓላማ አስጥሎ፣ ቤተ መንግስቱን አስፈርጥጦ፣ ኢትዮጵያችንን ጥሎ ወይም "በትኖ" እግሬ አውጭኝ የሚልበት አንድ ኃይል ከፊቱ ተጋርጧል። የወያኔ ጥይት ያልበገረው ኃይል። በሰው ልጆች የሚደርሰው ከፍተኛው የማሰቃየት ደረጃን የተላለፈ፣ ሞት ሕይወቱ የሆነ የሀገርና የሕዝብ ኃይል። ይህ በመቶ ሚልዮን የሚቆጠር በወያኔ እጅግ የተማረረና የቆሰለ፣ ልጆቹን ለአጋዚ ጥይት የገበረ፣ "ድምጻችን ይሰማ"ን ለእስር የዳረገ የሕዝብ ማዕበል በአራቱም ማዕዘን የወያኔን ውድመት ሊያፋጥነው እየነቀነቀው ይገኛል። ከፖለቲካ ድርጅት በላይ የሚፈራ ሕዝባዊ ኃይል።

ዛሬ ወያኔ በየትኛውም የሀገሪቷ አቅጣጫ የሕዝብ ጥላቻ ደርሶበታል። ወጣቶችን አምስት ለአንድ ቢጠነፍር ከሽፎበታል። ሠርቶ አደር ምስኪኖችን በገንዘብ ደልሎ በስለላ ቢያሰማራ የመከራው ተቋዳሾች ናቸውና አልሰራለትም። አንዱን ዘር ከሌላው በተለይ ኦሮሞና አማራ እርስ በርሳቸው ይተላለቁለት ዘንድ ገና ከጅምሩ የጠነሰሰው መርዝ ለወያኔ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች እንገንጠል ባይ ዘረኞች ጭምር ትምህርት ሊሆን የሚገባው የሁለቱ ጎሳዎች አንድነት በኢትዮጵያ ጥላ ሥር መሆኑን ያሳየ አኩሪ ተግባራቸው ሊከበር ይገባዋል። ኢትዮጵያ ያለ አማራ፣ ኢትዮጵያ ያለ ኦሮሞ፣ ኢትዮጵያ ያለ ትግራይ፣ ኢትዮጵያ ያለ ጉራጌ፣ ኢትዮጵያ ያለ ጋምቤላ፣ ኢትዮጵያ ያለ ኦጋዴን፣ ኢትዮጵያ ያለ አፋር፣ ኢትዮጵያ ያለ ልጆቿ ኢትዮጵያ አይደለችምና። የነኚህ ሁሉ እናት አንድ ኢትዮጵያ መሆኗን፣ በወያኔና በታኞቿ መቃብር ላይ የኢትዮጵያችንን የዘላለም ሕይወቷን ሊያድስ የሚያስችል ኃይልና ክብር በእጃቸው መሆኑን ሕዝባችን ከፖለቲከኞች በላይ እንደተረዳው ለ26 ዓመት ተከባብረውና ተስማምተው መኖራቸው በቂ ምስክር ነው።

ወያኔ/ህወሀት ዛሬ እራሱ በጠነሰሰው የቋንቋ ክፍፍል ኦሮሞም እንበለው አማራ የኢትዮጵያ ልጆች ከዳር እስከዳር ተነስተውበታል። ሥርዓቱ ዘረኝነት መለያው እንደሆነ ሕዝብን እጅግ በረሃብ በመቅጣትና በማደህየት፣ ለሀገርና ለሕዝብ ደንታ የሌለው የሀገር ምስጥ መሆኑ ከተነገረለት በትንሹ 26 ዓመታት አስቆጥሯል።

ወያኔ ዛሬ ትግራይን ገንጥሎ "ትግራይ-ትግሪኝ"ን ሊያቋቁም ነው ይባላል። ይህ ሊያስደንቅ አይገባውም "ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ያልቆጠረ፣ ኤርትራ ትገንጠልልኝ ብሎ ለተባበሩት መንግስታት ማመልከቻ ያቀረበ፣ ሰንደቅ ዓላማዋን ያዋረደ፣ ታሪክና ቅርሶቿን የናቀ ወያኔ መጨረሻው ሀገር መበታተን ቢሆን ምን ያስደንቃል?" ወያኔና ሻቢያ ከጥንስሳቸው "ኢትዮጵያ የ100 ዓመት ተረት ተረት ናት" ብለው መነሳታቸው መረሳት የለበትም። ደርግ በሀገርና በሕዝብ ልጆች ላይ የሠራውን ግፍ ተጠቅመው በጋራ ለሥልጣን ቢበቁም የሻቢያ ከወያኔ በስተጀርባ ኢትዮጵያን መቆጣጠር በሌላ አነጋገር የሌብነት፣ የዝርፊያ፣ የይገባኛል ጥያቄ "ሌባ ሲሰርቅ እንጂ ሲካፈል. . ." እንዲሉ ቢያለያያቸውም አሁንም በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ "የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች" ናቸው። በጥቅሉ የወያኔ/ህወሀት መጨረሻው ሽንፈት የሚጀምረው ትግራይን በመገንጠል ሳይሆን ዳግም ትግራይ በመመሸግ ይሆናል ቢባል ሚዛን ይደፋል።

የዛሬ አርባ ዓመት ለኢትዮጵያ አንድነት የቆሙትን አዳክሞና መትቶ ወያኔን ያጠናከረና የፈለፈለ ሻቢያ ዛሬም ከኢትዮጵያ የመገንጠል ዓላማ የሚያራምዱትን እጉያው አቅፎ ለቀጣይ መንግስትነት

የሚያዘጋጅ ለኢትዮጵያ አደጋ አቀጣጣይ ለመሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። እውነት ለመናገር የኢትዮጵያና የሕዝቧ አንድነት፣ የዓፄ ዮሐንስ መተማ፣ የአሉላ ዶጋሊ፣ የዓፄ ቴዎድሮስ መቅደላ፣ የምኒልክ ዐድዋ፣ የአርበኞቻችን ማይጨው ሲነሳ ወያኔና ሻቢያ እኩል ያማቸዋል። በወያኔና ሻቢያ አባባል ኢትዮጵያዊነትን ብሔራዊ ስሜት ለማዳከም ከጎሳ አማራ፣ ከሃይማኖት ኦርቶዶክስ፣ ከነገስታት ምኒልክ ዘራቸው፣ እምነታቸው፣ ታሪካቸው እንደቅደም ተከተላቸው መጥፋትና መበረዝ አለበት። ለዚህም ሂደታቸው ስኬታማነት አማራን ከጅምሩ በአርባ ጉጉና በደኖ በመጨፍጨፍ፣ ኦርቶዶክስ ሃይማኖትን አድባራት በማቃጠል፣ በመዝረፍና በስደተኝነት፣ ምኒልክን በ "ጡት ቆራጭነት" ሐውልት በመትከል የተደረገው ክንዋኔ ሀገራችን ህልውናዋን እንድታጣ በመንግሥት ደረጃ ከተቃጣባት የ26 ዓመታት መከራ ጥቂቶቹ ናቸው።

የኢትዮጵያ ንፁህ ሰብሎቿ በቅይጠ ሕይወታት የዓለም የምግብ ቁማር መርዛማ ድርጊት ተበክለዋል። ብቸኛ የጤፍ ሰብላችን ነዋይ ናፋቂው ወያኔ የባለቤትነቱን መታወቂያ ለባዕድ የሰጠበት ዘመን ላይ ደርሰናል። በተፈጥሮ ሃብቶቻችን ላይ፣ በታሪካዊ ቅርሶቻችን ላይ፣ በባህላችን ላይ የተያዘው የማጥፋት ዘመቻ ኢትዮጵያን ከመበታተን አንጻር የተከናወኑና እየተከናወኑ ያሉ ድርጊቶች መሆናቸውን መገንዘብ ሊያቅተን አይገባም። የምዕራብ ኢትዮጵያን አካባቢ ለሱዳን አሳልፎ የሰጠ፣ ከአንዱ ክፍለ ሀገር ወደሌላው በተለይ የትግራይን ግዛት ለማስፋት ከሌላው ቦጭቆ የወሰደ የወንበዴ መንግስት ቢኖር ወያኔ/ህወሀት ነው። ኢትዮጵያ ሀገራችን አምባገነንና ጨቋኝ ገዥዎች ቢገጥማትም ሀገር፣ ሕዝብ፣ ሰንደቅ ዓላማዋን፣ ታሪኳንና ባህሏን ሊያጠፋ የነገሰባት አገዛዝ ቢኖር ከዮዲት ጉዲትና ከግራኝ አህመድ/መሐመድ በቀጣይነት ወያኔ/ህወሀት መሆኑ ታሪኳን ልዩ ያደርገዋል።

"ኢትዮጵያ" ካልን ትግራይ ተገንጥላ ኢትዮጵያ እንደማትኖር ልንገነዘብ ይገባል። "ኢትዮጵያ" ካልን እንደ ወያኔና አንዳንድ ዘረኞች አባባል "ኦሮምያ" ሀገር ልትሆን አትችልም። አማራ ብቻዬን ካለ ሀገር ምኑን ኢትዮጵያ ሆነች? ኢትዮጵያ ያሏት ጎሳዎችና ቋንቋ ተናጋሪዎች ኦሮሞ፣ አማራና ትግራይ ብቻ ናቸውን? በነኚሁ ጎሳዎች መካከል በርካታ አንድነቶችንና ልዩነቶችን ኢትዮጵያ ይዛ መቆየቷ ይዘነጋልን? እውን ሀገራችን ያጣችው የጎሳዎች እርስ በርስ መበዳደል ነው ወይስ የአገዛዝ በደል? እውን ሀገራችን ያጋጠማት የቋንቋ ችግር ወይስ ሕዝባዊ አስተዳደር? በጥቅሉ የሀገራችን ችግር ለሁሉም ጎሳዎችና ነገዶች እስከዛሬ መልስ ያላገኘው ገደብ የሌለው የዜግነት ዴሞክራሲያዊ መብት ጉዳይ ነው። አማራው በኦሮሞ ባህል እንደሚኮራ፣ የትግሬው ሃይማኖት የኢትዮጵያ መሆኑ፣ የኦሮሞ ጋብቻ ኢትዮጵያዊ መሆኑ፣ የጉራጌ ምርቃት ለሀገር መሆኑን፣ የጋምቤላ ሀገር ፍቅር የሁላችን መሆኑን፣ ወዘተ መገንዘብ ይኖርብናል።

የወያኔ ጥፋት በሀገርና ሕዝብ የመጣ መሆኑን የተረዳን ዜጎች ኢትዮጵያን ለማዳንና አንድነቷን ለማስጠበቅ ከእኛ ከልጆቿ ሌላ ማንም እንደማይመጣ ቁርጡን ልናውቅ ይገባል ስንል "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" አበክረን እናስገነዝባለን።

ማንም የውጭ ኃይል ለራሱ ጥቅም የቆመ ነውና ልመናችን ገደብ ሊኖረው ይገባል። በዐድዋ ነፃነቷን የተቀዳጀችና የሊግ ኦፍ ኔሽንስ (የሕዝቦች ጉባኤ) መሥራች ኢትዮጵያ ዳግም በማይጨው ጦርነት ስትወረር በፉጨት ያደመቁ መንግስታት ዛሬም አልተኙልንምና አንታለል። በ1981 ዓ.ም. የለንደን ድርድር ወያኔን "ግባ!" ብሎ ትዕዛዝ የሰጠ አደራዳሪ ወያኔን ይተካለት ዘንድ የሚፈልገው ሀገሪቷን እንደልቡ ሊቆጣጠራት የሚያስችለው ተተኪ ፈረስ ነውና ለሀገራችን የመፍትሄው ቁልፍ ከራሳችን ሌላ ማንም ሊኖር እንደማይችል አበክረን እንመርምር።

ወያኔ/ህወሀት ሀገራችን ኢትዮጵያን በተመለከተ የመጨረሻው ተግባሩ በተደጋጋሚ ቢባልም "ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" እንደ ፖለቲካ ድርጅት ዛሬ ጊዜው ደርሷልና ማስገንዘብ የምንፈልጋቸው ጉዳዮች፦

የመጀመሪያው ፦ የኢትዮጵያ ሀገራችንን አንጡራ ሀብት በመዝረፍና የተለያዩ ኅሳዎቿን እርስበርስ በማጋጨት፣ የሃይማኖት ጥላቻን በመንዛት፣ ታዳጊ ሕጻናትንና ወጣቶችን የአደንዛዥ ዕጽ ሱሰኛ በማድረግና ትውልድ በማቀጨጭ፣ አኩሪ ሰብሎቻችንን በማምከንና በመጤ መርዘኛ ዘሮች በመተካት፣ በተለይ ያነጣጠረበትን የአማራ ዘር ሴቶችን መካን በማድረግ፣ ሕፃናትንና ሴቶች እህቶቻችንን ለተለያየ ወሲባዊ ተግባራት ለውጭው ዓለም ሳይቀር በመሸጥ፣ በመጠኑ ከትግራይ የከተማ አካባቢዎች ሌላ ሁሉንም የሀገሪቷን ክፍሎች በማራቆትና በማደህየት ሕዝባችንን እያሰቃየ የመግዛት ዘመኑ ዛሬ የመጨረሻው ደረጃ ደርሷል፣

ሁለተኛው፦ ወያኔ/ህወሀት ኢትዮጵያን "እንደፈጠራት"ና እንደሚፈልጋት ማስተዳደር ከተሳነው ያለው ሌላ አማራጭ ትግራይን በመገንጠልና ከፈጣሪው ሻቢያ ጋር በመደራደር ሲመሠረቱ የነበራቸውን "ትግራይ-ትግሪኝ" ምሥረታ እውን በማድረግ ሌላውን የሀገሪቷን ክፍል በሚቻላቸው አቅም በኅሳና በሃይማኖት በማተራመስና እርስ በርስ ይጋጩ ዘንድ የፈለፈሏቸውን ዘረኞች በመርዳት ሌላውን የኢትዮጵያ ግዛት የእርስ በርስ ሽኩቻ ውስጥ በመዘፈቅ ይበታተንላቸው ዘንድ መጣር፣

በሦስተኛ ፦ ደረጃ በእነሱ አምሳያ ወያኔ/ህወሀትን ማዕከል ያደረገ ዘረኛ ኢሕአዴግን መሥርተው ኢትዮጵያን ለ26 ዓመታት እንዳተራመሱ ሁሉ ቀጣዩ መንግሥት በለውጥ ስም ሌላ ዳግም በዘር የተደራጀ ኃይል ስብስብ በመሆንና እንደ ኤርትራ "ነፃነት ወይስ ባርነት" የትግራይን መገንጠል እውቅና በመስጠት ሌላው የሀገራችን ግዛት በተረኛ ዘረኛና አምባገነን እርስ በርሱ ሲተራመስ ከዳር ሆነው ለማላገጥና ለማዳከሙ ተባባሪ ለመሆን ሌላው ዕቅዳቸው ይሆናል። ለዚህ ደግሞ የኢትዮጵያን አንድነት ለማይፈልጉ፣ የተዳከመች ኢትዮጵያን እንደልባቸው ለመቦጥቦጥ ላሰፈሰፉ፣ ኢትዮጵያን ለሚፈልጉት ስትራቴጂካዊ ጥቅማቸው ሃይ ባይ እንዲኖርባቸው ለማይፈልጉ ከባቢና "ኃያላን" መንግሥታት ሀገሪቷን አሳልፎ በመስጠት ድጋፍ ለማግኘት እንደሚጥሩ መገመት አስቸጋሪ አይሆንም።

ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብና የፖለቲካ ድርጅቶች ሆይ!

"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" በወያኔ/ህወሀት 26 ዓመታት የግፍና የዘረኝነት አገዛዝ ጠንክሮ የተነሳና የተዘጋጀ ሀገር አድን ሕዝባዊ የፖለቲካ ድርጅት መኖር እንደሚገባው እናምናለን። ዛሬም እንደትላንቱ በሀገራችን ውስጥ እየተቀሰቀሰ ያለው አካባቢያዊ እንቅስቃሴ ሀገራዊ መልክ ይዞ ወያኔ/ህወሀትን ድምጥማጡን ቢያጠፋው ቀጣዩ መንግስት አሳሳቢ ነው። ሕዝብን ማደራጀትና ማሰባሰብ ለአለፉት 26 ዓመታት ጥረት ቢደረግም የተሳካ ውጤትና አካሄድ አልታየም። ዛሬ እንኳን ሕዝብን ለማደራጀት እርስ በርስ በጋራ አጀንዳ ላይ ተስማምቶና ተነጋግሮ ለተደረጉ ጥፋቶች ይቅር ተባብሎ ለመምከር ዝግጁነት ሳይኖር ሕዝባዊ ማዕበል ሊቀሰቀስ እንደሚችል ስለሚገመት ነው ማንም ቀጣዩን መንግሥት በእርግጠኝነት መናገር የተሳነው። ዛሬ ባለድል ከሆን እሰየው ሠርገኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ መጥቷል፤ ለበርበሬው ቅንጠሳ እንኳ የተዘጋጀ ኃይል የለም ቢባል ድፍረት አይደለም።

አሁንም በአለው የተጣበበ ጊዜ ትንሽም ቢሆን ለሕዝባዊ ትግሉ ሊደረስ የሚቻለው በጋራ በመሰባሰብ በመሆኑ ትኩረት ልንሰጠው ይገባል። ፖለቲከኛው ተባበረ አልተባበረ ሕዝባዊ ዐመጹ አይቀሬነቱ

ምልክቱን እያሳየ ነውና። ከነጎድጓዱ በፊት የብርሃን ወጋጋኑ እየታየ ነው። የሥልጣኑ ባለቤት ሕዝብ ያልሆነበት ዳግማዊ የካቲት ይታያልና። ሕዝብ ይታገላል እንጂ የትግል መሪና አስጠባቂ ለመሆን መደራጀት ግድ ነው። ይህንን ሕዝባዊ ትግል መና አናስቀረው። ይህንን ክፍተት በአለቀ ሰዓት ማጥበብ ባይቻል እንኳ የሁሉም ፖለቲካ ድርጅቶች በተለይ በኢትዮጵያና በሕዝቧ አንድነት ጽኑ መሠረት ያለን ለሕዝባዊ ትግሉ በጋራ እንነሳ ስንል "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" ጥሪያችንን እናሰማለን።

ባላሰለሰ ጥረት በተለያየ አካባቢ የወያኔ/ህወሀት ሥርዓት መወገድን እውን ለማድረግ ከዱላ፣ እስርና ጥይት ጋር እየተጋፈጣችሁ ለምትፋለሙ የኢትዮጵያ ልጆች ምስጋናችንና ክብራችን የላቀ ነው። ለሀገርና ለሕዝብ አንድነት ሲባል ያለምንም ጥርጥር የወያኔ/ህወሀት የግፍ አገዛዝ ማብቃት ያለበት የተጀመረው አካባቢያዊ ንቅናቄ ሀገራዊ መልክ ሲይዝ መሆኑን ልናስገነዝብ እንወዳለን። ለዚህም በተለይ በተለያዩ አማራና ኦሮሞ የኢትዮጵያ ልጆች እየተቀጣጠለ ያለው ፀረ-ወያኔ አመጽ መቀናጀትና ሌሎችም ጎሳዎች "ትግላችሁ ትግላችን" ብላችሁ ልታደምቁት ይገባል።

በተለይ ኦሮሞና አማራ ጎሳዎችን ወያኔ እርስ በርስ ሊያፋጃቸው ያልፈነቀለው ድንጋይ ያላደረገው ጥረት የለም። ማንነቱን የሚያውቀውና ተከባብሮ ለዘመናት ኢትዮጵያን በደምና አጥንቱ ያኖራት የሁለቱ ጎሳዎች ኅረተሰብ በጋራ ዋናው ጠላቱ ወያኔ ላይ በማነጣጠር ያለውን የወያኔ ሥርዓት እያናጋ በአለበት በአሁኑ ወቅት በኢሉባቡር ክፍለ ሀገር ቡኖ በደሌ አውራጃ የኦሮሞ ጎሳ በአማራው ወገኑ ላይ ጭፍጨፋ እንደፈጠረ ተደርጎ በመሠሪ የወያኔ ሰርጎ ገቦች በተፈጠረው ዘግናኝ ጭፍጨፋ የፈሰሰው የንፁሃን ወገኖቻችን ደም እጅጉን አሳዝኖናል። ወያኔ ዛሬ የመጨረሻው ዕብደት ላይ ነውና ገና ምንም ከማድረግ አይመለስምና ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የወያኔ የዘርና የክልል መስመር ሳይገድበው ሁሉም ከሁሉ በኢትዮጵያዊነቱ ሀገሩን ማዳን ይኖርበታል እንላለን። የመጨረሻው የድል ባለቤት ኢትዮጵያ ነችና ያን ጊዜ በከንቱ የፈሰሰው የልጆቿ ደም ከመቃብር በላይ ይጮኻል! የፍትህ ያለ ይላል! ያኔ ይብላኝ ለዘረኛው ወያኔና ለአጃቢዎቻቸው እንላለን።

ዛሬ ኢትዮጵያ ሀገራችንን ከወያኔ የመበታተን ቅዠትና ህልም ልናድን የምንችለው እኛው ቆራጥ ልጆቿ ነንና የተጀመረው ሕዝባዊ ንቅናቄ ለወያኔ መውደም የመጨረሻው መሆን ይኖርበታል። በወያኔ/ህወሀት መሠሪ ተንኮል ሳንደናገጥና ሳንበገር ትግሉ በአንድነት ይፋፋም። ለሀገርና ሕዝብ የሚከፈል መስዋዕትነት ክቡር ነውና ሀገር በልጆቿ ትኩራ! ስማችሁ በታሪክ ዘላለማዊነት ይኖረው ዘንድ ታሪክ ሠርታችሁ ኢትዮጵያን እናድናት ስንል "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" ከጎናችሁ መሆናችንን አበክረን እናሳውቃለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!
እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!!!
"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"

**ጥቅምት** 16 **ቀን** 2010 **ዓ.ም**. (October 26, 2017)

**<u>ማሳሰቢያ ፡</u>**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" «***ኢትዮጵያችን***» ዕትም በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" በቅርቡ መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org

ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachen